የቀድሞው የኢትዮጵያ አትሌቶች በታላቋ ብሪታኒያ።
**Former Ethiopian athletes in United Kingdom.**

ለ...........................

ቀን 25/03/2025

ጉዳዩ፡- እስፖንሰርሺፕን ይመለከታል።

እኛ በእንግሊዝ ሀገር የምንኖር የቀድሞው የኢትዮጵያ አትሌቶች በማህበር ተደራጅተን ባለፉት ሦስት ዓመታት በሰኔ ወር የአድዋ
ድል 5 ኪሎ ሜትር እና የታላቁ ሩጫን በለንደን 10 ኪሎ ሜትር በህዳር ወር  አዘጋጅተን እንደነበረ ይታዎሳል: ይህን አስመልክቶ በዝግጅቱ የተሳተፉት እና እንድሁም ያልተሳተፉትም ጭምር የውድድሩን ውጤታማነትና ጠቀሜታ በመገንዘብ ወደፊትም በዚሁ መልክ እንድንቀጥልበት ብዙ አስተያዬቶች እየደረሱን በመሆኑ የአትሌትክስ ቡድኑም የህዝቡን ፍላጎትና ስሜት ከግምት ውስጥ በማስገባት በይበልጥ በመደራጀትና በመዘጋጀት
የአድዋ ድል የቤተሰብ አዝናኝ ዝግጅትና  የ5 ኪሎሜትር የሩጫ ውድድርን ዳግም በሰኔ 21/2017 (June 28/2025 ለማዘጋጀት መወሰናችንንና ዝግጅቱም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ መሆኑን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው:

የዚህ ዝግጅት ዋና አላማውም፡-

1, የማህበረሰቡን የስፖርት ፍላጎት ለማሟላትና ፍላጎትም እንዲኖረውና የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርግ ለማበረታታት
2, የሩጫ ውድድሮችን በማዘጋጀት ኮሚኒቲው አድስ የስፖርት ባህልን እንዲያዳብር ለማድረግ
3, በሩጫ ውድድ አሸናፊ የሚሆኑትን ወጣቶች ደግሞ ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ ክትትልና የምክር ድጋፍ ለማድረግ
4, በአትሌቲክስ ጥሩ ተሳትፎ ያላቸውን ወጣቶች ክለብ ደረጃ ተመዝግበው ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ምክርና አቅጣጫውን ለመስጠት
5, አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የስልጠናና የምክር አገልግሎትን ለመስጠት
6, የኢትዮጵያ አትሌቶች በአለም ላይ ውድድር ሲያደርጉ ውጤታቸውን ተከታትለን በመገናኛ መረባችን ለማህበረሰቡ ለማሳዎቅ
7, በአጠቃላይ ማህበረሰባችን የስፖርት ግንዛቤና ጥቅም እንዲያቅና ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ነው::

ስለዚህ በዚህ በአይነቱ የተለየና አዝናኝ በሆነው የሩጫ ውድድር በተሳካና ደማቅ በሆነ መንገድ ለማዘጋጀት እንድንችል የእርስዎ እርዳታና ትብብር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ እስፖንሰርሽፕ እንዲያደርጉንና በዝግጅቱም በመሳተፍ እንዲያግዙን በአክብሮት እንጠይቃለን የእርስዎንም ድርጅት በዚሁ በርካታ ሰዎች በሚገኙበት የሩጫ ቀን በሰፊው የማስተዋውቅ ዕድሉን
ይጠቀሙበታል።  ድርጅትዎን የበለጠ ለማስተዋወቅ የድርጅትዎን ሥምና ዐርማ በሁሉም ማስታወቂያዎቻችን ላይ እናስቀምጣለን። በዕለቱም ሥሙ እየተጠራ እንዲነገር እናደርጋልን።

የእስፖንሰር አይነቶችም እንደሚከተሉት ናቸው።

አንደኛ ደረጃ እስፖንሰር --------- ወርቅ £
ሁለተኛ ደረጃ እስፖንሰር -------   ብር £

በዚህ ዝግጅት ላይ የእርሶዎንና የድርጅቶዎን አሻራ እንደሚያስቀምጡ ተስፋ እያደረግን የዝግጅቱ ቀን እየተቃረበ በመሆኑ ፈቃድዎትን በቶሎ እንዲያስታውቁን እየጠየቅን ስለሚያደርጉልን ትብብር ምስጋናችን የላቀ መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት ለመግለጽ እንወዳለን።

የቀድሞው የኢትዮጵያ አትሌቶች ማህበር በታላቋ ብሪታንያ።
**Phone number 07456999348**
**Email.** eainuk2@yahoo.com

Former Ethiopian Athletes in the United Kingdom

Date: 25/03/2025

Subject: Sponsorship Request

We, the former Ethiopian athletes residing in the United Kingdom, have been organising community events for the past three years. Every June, we host the Adwa Victory 5K Run, and every November, we organise the Great Run London 10K. Based on the feedback we received from both participants and non-participants, it is evident that these events are highly valuable and impactful. Many people have expressed their interest in seeing these races continue. In response to this demand, our athletics group has decided to organise the Adwa Victory Family Fun Event and 5K Race again on June 28, 2025. We are delighted to share that preparations for this event are progressing well.

Objectives of the Event:

1. To promote sports participation within the community and encourage people to stay active.

2. To develop a new sports culture within the community through organised running events.

3. To provide support and mentorship for young runners to help them achieve better results.

4. To assist talented and young athletes in joining professional clubs and developing their skills.

5. To offer training and advisory services when necessary.

6. To follow and promote the achievements of Ethiopian athletes in global competitions through our communication network.

7. To enhance public awareness and engagement in sports for the benefit of the entire community.

Sponsorship Opportunity

To ensure the success of this exciting and meaningful event, we kindly request your support through sponsorship. By sponsoring this event, your organisation will have the opportunity to gain wide exposure on race day, where many people will be present. We will prominently display your company’s name and logo on all event promotional materials. Additionally, your organisation’s name will be mentioned throughout the event.

Sponsorship Categories:

• Gold Sponsor – £1,000

• Silver Sponsor – £500

We sincerely hope for your support and partnership in making this event a success. As the event date approaches, we kindly ask you to confirm your sponsorship at your earliest convenience. We hugely appreciate your cooperation and generosity.

Former Ethiopian Athletes Association in the United Kingdom

Phone: 07456999348

Email: eainuk2@yahoo.com